MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# 5/6 ክፍል የ2ኛ ማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የወላጅ መመሪያ

በማርክ መስጫ 2 ወቅት የ 5/6 ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በ *በኢታሊክስ* የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### የቁጥር ስርአት

- የክፍልፋዮችን ድርሻዎች መተርጎምና ማስላት፣ እና ፕሮብሌሙን ለመወከል በሚታዩ የክፍልፋይ ሞዴሎችና ቀመሮች በመገልገል፣ ክፍልፋዮችን በክፍልፋዮች ማካፈልን በማካተት የቃል ፕሮብሌሞችን መፍታት።
- በመደበኛ ቀመር በመጠቀም በቀልጣፋነት ባለበርካታ-ዲጂት ቁጥሮችን ማካፈል።
- ለያንዳንዱ ግብረት ደረጃውን በጠበቀ የስሌት ዘዴ በመጠቀም፣ ባለ-በርካታ-ኣሃዝ ዴሲማሎች መደመር፣ መቀነስ፣ ማባዛት፣ እና ማካፈል።

### ንጥጥር እና የተመጣጠነ ግንኙነቶች

- የንጥጥርን ፅንሰሃሳብ መገንዘብ እና በሁለት መጠኖች/ብዛቶች መካከል ኣንድ የንጥጥር ዝምድና ለመግለፅ በንጥጥር ቋንቋ መገልገል።
- $b \neq 0$ ሁኖ የa/b ኣሃዱ ዋጋ/ሚዛን ከ a:b ንጥጥር ጋር የመዛመድ ፅንሰሃሳብን መገንዘብ፣ እና በንጥጥር ግንኙነት ኣውድ ውስጥ የመጠን ቋንቋን መጠቀም።
- ስለ አቻ/ተመጣጣኝ የንጥጥሮች ሠንጠረዥ፣ የቴፕ ስእሎች፣ የእጥፍ ቁጥር መስመር ስእሎች፣ ወይም ስለ ቀመሮች ምክንያት በመስጠት፣ በንጥጥር እና በዋጋ/ሚዛን ኣመክኛኘት ተጠቅሞ የተጨባጭ-ኣለም እና የሂሳብ ፕሮብሌሞችን መፍታት ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- ኣንድ ፅሁፍ በትክክል ምን እንደሚል ሲገልፁ እና ከፅሁፉ ጥቅሶች ሲያወጡ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- የኣንድ ታሪክ፣ ድራማ፣ ወይም ቅኔ ዘውግ ከፅሁፉ ዝርዝሮች መወሰን፣ በኣንድ ታሪክ ወይም ድራማ ገፀባህርያት ለፈተናዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ወይም በግጥም ወስጥ ተናጋሪ ኣንድ ርእስ ላይ እንዴት እንደሚያንፀባርቅ በማካተት፤ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- በኣንድ ታሪክ ወይም ድራማ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ገፀባህርያት፣ ሁኔታዎች፣ ወይም ክውነቶችን ማወዳደርና ማነፃፀር፣ በፅሁፉ ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ዝርዝሮች በመውሰድ።
- ተከታታይ ምእራፎች፣ ትእይንቶች፣ ወይም የግጥም ስንኞች/ስታንዛስ አንድ ላይ ተስማምተዉ ለተለየ ፅሁፍ እንዴት ኣጠቃላይ መዋቅር እንደሚሰጡ ማብራራት።
- የኣንድ ተራኪ ወይም ተናጋሪ ኣስተያየት በክውነቶች አገላለጽ ላይ እንዴት ተፅእኖ እንደሚያደርግ መግለፅ።
- የሚታዩ እና የበርካታ-ሚድያ ንጥረ ነገሮች ለኣንድ ፅሁፍ ትርጉም፣ ድምፀት፣ ወይም ውበት እንዴት ኣስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ መተንተን።

- *በተመሣሣይ ፍሬ ነገሮች እና ርእሶች ላይ የተነገሩ ታሪኮችን ስለአቀራረባቸው እያነፃፀርክ/ሽ አወዳድር/ሪ።*
- *በ5ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን ኣንብቦ መገንዘብ።*

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- የኣንድን ፅሁፍ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዋነኛ ኣስተሳሰቦች መወሰን እና በቁልፍ ዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፉ ማብራራት፤ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- በኣንድ ታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ወይም ቴክኒካዊ ፅሁፍ ውስጥ የተለየ መረጃ ላይ የተመሰረተ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ግለሰቦች፣ ክውነቶች፣ ኣስተሳሰቦች፣ ወይም ፅንሰሃሳቦች መካከል የሚገኙ ዝምድናዎችን ወይም ግንኙነቶችን ማብራራት።
- ከ 5ኛ ክፍል የማስተማርያ ጽሑፍ ላይ አጠቃላይ የትምህርት ቋንቋ እና የሙያ/የአስተሳሰብ/የድርጊት ቃላትን እና ሃረጎችን ትርጉም ለይተህ/ሽ አሳይ።
- ከአንድ ወይም ከሁለት ጽሑፍ ላይ አጠቃላይ የድርጊቱን ቅንብር፣ ሃሳቦችን፣ ፅንሰሃሳቦቹን፣ ወይም መረጃ/ኢንፎርሜሽን አወዳደር/ሪ እና አነፃጽር/ሪ።
- በሚወክሉት ኣስተያየት ውስጥ ኣስፈላጊ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን እያመላከቱ፣የተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ በርካታ ትረካዎችን መተንተን።
- ለጥያቄ በፍጥነት/ቶሎ መልስ የማግኘት፣ ወይም ችግርን/ፕሮብሌምን በብቃት የማቃለል ችሎታህ(ሽ)ን ለማሳየት ከተለያዩ ህትመቶች ወይም ዲጂታል ምንጮች መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግኝ/ኚ።
- አንድ ደራሲ በፅሁፍ ውስጥ የተለዩ ነጥቦችን ለመደገፍ ምክንያቶችንና ማስረጃ እንዴት ኣገልግሎት ላይ እንዳሚያ(ምታ)ውል ማብራራት፣ የትኛው ምክንያትና ማስረጃ የትኛውን ነጥብ/ቦች እንደሚደግፍ በመለየት።
- *መረጃዎችን በተመሳሳይ ርእስ ከበርካታ ፅሁፎች ማዋሃድ ስለ ርእሱ በኣዋቂነት ለመፃፍ ወይም ለመናገር እንዲቻል።*
- *ለ5ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።*

### ቋንቋ፡- የቃላት ዝርዝር ግኝት እና ኣጠቃቀም

- በ5ኛ ክፍል ርእሶችና ፅሁፎች በትብብሮሽ ውይይት መስከ በውጤታማነት መሳተፍ፣ በሌሎች ኣስተሳሰቦች ላይ በመገንባት እና የግልን በጥራት እየገለፁ።
- ድምፅ ከፍ ተደርጎ የተነበበ ፅሁፍን ወይም በተለያዩ ሚድያና፣ በሚታይ፣ የብዛት እና የቃልን የሚያካትቱ ቅርፀቶች የቀረበ መረጃን ማጠቃለል።

- በ5ኛ ክፍል ምንባብ በመመስረት ያልታወቁና ባለ-በርካታ-ትርጉም ቃላቶችንና ሃረጎችን ትርጉም መወሰን ወይም ማብራራት።
- የዘይቤያዊ ኣነጋገር፣ የቃል ዝምድና፣ እና በቃል ትርጉሞች ውስጥ የሽሙጦችን ግንዛቤ ማሳየት።
- የክፍል-ተገቢ ኣጠቃላይ ኣካዴሚያዊና ባለ-ልዩ-መስክ ቃላቶችና ሃረጎች፣ ንፅፅር፣ መደመር፣ እና ሌሎች ሎጂካዊ ዝምድናዎችን (ለምሳሌ፣ የሆነ ሆኖ፣ ምንም እንኳን፣ ቢሆንም፣በተመሳሳይ፣ በተጨማሪ) የሚያካትቱ ማወቅ/ማግኘትና በትክክል ኣገልግሎት ላይ ማዋል።

## ጽሑፍ

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- ኣንድን ርእስ ለማገናዘብና እስተያየቶችንና መረጃዎችን በግልፅ ለማስተላለፍ መረጅያዊ/ገላጭ ፅሁፎች መፃፍ።
- ኣንድ ርእስ በግልፅ ማስተዋወቅ፣ ኣጠቃላይ ትዝብት እና ትኩረት መስጠት፣ ርእሱን በሃቆች፣ ፍቺዎች፣ ጭብጥ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ እና ከቡድን ጋር በተዛመዱ መረጃዎች በሎጂክ ማዳበር፤ ቅርፀት (ለምሳሌ፣ ኣርእስቶች)፣ ስእሎች፣ እና በርካታ-ሚድያ ግንዛቤን ለማገዝ ጠቃሚ ሲሆን ማካተት።
- አርእስቱን ለማስተዋወቅ ወይም ለመግለጽ ትክክለኛውን ቋንቋ እና የድርጊቱን-ቃላት ተጠቀም/ሚ።
- ከቀረበው መረጃ ወይም ማብራርያ ጋር የተዛመደ ማጠቃለያ ኣረፍተሃሳብ ወይም ክፍል ማቅረብ።

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር ውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካዎችን መጻፍ።
- ተሞክሮዎችንና ክውነቶችን ለማዳበር ወይም የገፀባህርያትን ምላሾች ለሁኔታዎች ለማሳየት፣ ውይይት፣ ገለፃ፣ እና እርምጃ በመሳሰሉ የትረካ ቴክንኮች መጠቀም።
- የክውነቶችን ኣፈፃፀም ተራ ለማስተዳደር በተለያዩ የሽግግር ቃላት፣ ሃረጎች እና ኣንቀፆች መገልገል።
- ከተተረኩ ተሞክሮዎች ወይም ክውነቶች የሚከተል ኣንድ መደምደሚያ ማቅረብ።

**አስተያየት**

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድ ርእስ ወይም ፅሁፍን በጥራት ማስተዋወቅ፣ አስተያየት ማስቀመጥ፣ እና አስተያየቶች በሃቆችና በዝርዝሮች የተደገፉበት፣ እና የፀሃፊውን አላማ ለመደገፍ በሎጂክ የተመደቡበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።
- በቃላቶች፣ ሃረጎች፣ እና በአንቀፆች (ለምሳሌ፣ በተከታይ፣ በተለይ) በመጠቀም አስተሳሰብንና ምክንያቶችን ማገናኘት።
- ከቀረበው ሃሳብ ጋር የሚገናኝ ማጠቃለያ/የመደምደሚያ ሃሳብ መግለጫ ስጥ/ጪ።

**ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር**

- እድገቱና አደረጃጀቱ ለተግባር፣ አላማ፣ እና ለአድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮችና ከአውቂዎች አመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፕላን፣ ክለሳ፣ አርትእ፣ ዳግመ-ፅሁፍ፣ ወይም አዳዲስ ሙከራ እንደአስፈላጊነቱ በማድረግ፣ ፅሁፍን ማዳበርና ማጠናከር።
- መረጃዎችን በማስታወሻዎች እና ባለቀ ስራ ማጠቃለል ወይም በሌላ አባባል ማስቀመጥ፣ እናም የምንጮች ዝርዝር ማቅረብ።

- ትንተና፣ አስተሳሰብ፣ እና ምርመራን ለመደገፍ ከስነፅሁፍ ወይም ከመረጃያዊ ፅሁፎች ማስረጃ መውሰድ።
- ለተለያዩ በዲሲፕሊን-የተወሰኑ ተግባራት፣ አላማዎች፣ እና አድማጮች/ታዳሚዎች በተራዘም የጊዜ መቃኖችና አጫጭር የጊዜ መቃኖች በድግግሞሽ መፃፍ።

**የቋንቋ አጠቃቀም**

- አንድ ርእስ ላይ ወይም ጽሑፍ ላይ ሪፖርት ወይም አስተያየት አቅርብ/ቢ፣ የሃሳቦችን ቅደምተከተል በመጠበቅ እና ተጨባጭነታቸውን እና ዋና ዋና ሃሳቦችን ወይም መሪ ሃሳቦችን በተገቢ ዝርዝር በማስደገፍ ለመረዳት በሚያስችል ሁኔታ ተናገር/ሪ።
- አስፈላጊ ሲሆን ዋናውን ሃሳብ ወይም ፍሬ ነገሩን ለማዳበር መገናኛ ብዙሃን መገልገያዎችን እና በዓይን የሚታዮ ነገሮችን ጨምረህ/ሽ አቅርብ/ቢ።
- እንግሊዘኛን ሲፅፉ ወይም ሲናገሩ ደረጃውን የጠበቀ የእንግሊዘኛ ስዋስው እና አጠቃቀም፣ እና ሲፅፉ ካፒታላይዜሽን፣ ስርአተነጥብ፣ እና የፊደል አመራረጥ ችሎታ ማሳየት።
- ለትርጉም፣ ለአንባቢ/አድማጭ ፍላጎት፣ እና ለዘየ አረፍተነገሮችን ማስፋፋት መገጣጠም፣ እና መቀነስ።

## ሳይንስ

**መሬትና የህዋ ሳይንሶች**

- መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማስተላለፍ ቅጥ/ቅደምተከተል የሚጠቅሙ በርካታ መፍትሔዎችን ፍጠር(ሪ) እና አነፃፅር(ሪ)።
- ቅርፀቶችን ከምገድ ርዝመት እና ከመጠን አኳያ ለመግለፅ እና ማእበሎች ነገሮችን እንዲንቀሳቀሱ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ የማእበሎች ሞዴል ማዳበር።
- ከአንድ ቁስ አካል የሚያንፀባርቅ ብርሃን ወደ ዓይን ሲገባ/ሲያንፀባርቅ ቁስ አካሉ እንዳይታይ እንደሚያደርግ ናሙና አዘጋጅተህ(ሽ) አስረዳ(ጂ)።
- በቁስ አካላት ላይ መሬት የምትጠቀመው የስበት ኃይል ወደታች/ቁልቁል ይስባል የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሃሳብ ስጥ(ጪ)።
- በቁስ አካላት ላይ መሬት የምትጠቀመው የስበት ኃይል ወደታች/ቁልቁል ይስባል የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሃሳብ ስጥ(ጪ)።

**ኢንጂነሪንግ ንድፍ እና ሂደት**

- አንድን ችግር/ፕሮብሌም እና የችግሩን ይዘት/ውስብስብነት ጭምር በተቻለ መጠን ለመፍታት የሚያስችል መመዘኛ እና የተለያዩ መፍትሔዎችን በማወዳደር/በማነፃፀር ለእያንዳንዱ መፍትሔዎችን አፍልቅ(ቂ)።
- ለስኬታማነት የተወሰነ መስፈርትን እና የቁስ፣ የጊዜ፣ እና የወጪ ገደብን ያካተተ አንድ ፍላጎትን ወይም መሻትን የሚያንጸባርቅ ቀላል ንድፍ ፕሮብሌም መግለጽ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

**የስነ-ዜጋ ትምህርት**

- ግለሰቦችና ቡድኖች ለሜሪላንድ የፖለቲካ ስርአት እንዴት አስተዋፅኦ እንዳደረጉ መተንተን።
- የሜሪላንድ አስተዳደር የግለሰቦችንና የቡድኖችን መብቶች እንዴት እንደሚከላከል መግለፅ።
- የመንግስትን ቀደምት መሰረቶች፣ ተግባሮች፣ እና አላማዎች ማገናዘብ።
- የፖለቲካዊ ስርአቶቻችን መሰረቶች የሆኑትን ታሪካዊ ክውነቶች፣ ሰነዶች፣ እና ልምዶች መተንተን።
- ህዝባዊ መመርያና ጉዳዮችን በሚመለከት የቅኝ ግዛት መንግስትን ሚናዎች መተንተን።
- የግለሰብ ሚናዎችና አስተያየቶች የአሜሪካን ፖለቲካዊ ስርአት እንዴት እንደሚቀርፁ መተንተን።
- እንደ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ የሲቪል ተሳትፎን አስፈላጊነት መተንተን።
- በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ግላዊ መብቶችንና ግዴታዎችን መግለፅ።
- የህጋዊነት መርህ ማገናዘብ።

**ባህል**

- የተለያዩ የሜሪላንዳዊዎች አስተያየቶች ስምምነት እና/ወይም ግጭ መቀስቀስ እንደሚችሉ መገምገም።
- በቅኝ ግዛት ዘመን በዝምድናዎች/ግንኙነቶች ላይ ተፅእኖ ያደረጉ ታሳቢዎችን መተንተን።

**ታሪክ**

- የአሜሪካን ርዕዮት የፈጠረውን/ያስከተለውን ተፅእኖ ተንትን(ኚ) በዝርዝር አስቀምጥ(ጪ)።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ጥያቄዎችን መፍለቅና ማሻሻል።
- የመረጃ ተፈላጊ ለማሟላት መገልገያዎችን መለየት።
- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት የተቀረፀ/የተመዘገበ ውሂብ/መረጃ ጥራት መገምገም እና መተንተን።
- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን ካሉበት ፈልጎ ማግኘት፣ መገምገም፣ እና መምረጥ።
- ሃሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ።
- የተፈላጊ መረጃን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

**የሥነጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት**

- ለስነጥበብ ሥራ የፈጠራ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ ሃሳቦችን አጠናቅር(ሪ)።
- ሃሳብን፣ ስርአተ ሒደት፣ ወይም ውጤት ለማስተላለፍ፣ የስነጥበብ መሠረታዊ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም(ሚ)።
- የእደጥበብ መሥሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና የሥራ ቦታን ለመጠቀም ተገቢውን የሥነጥበብ መሥሪያ ዘዴዎችን/ቴክኒኮችን እና ሥርአቶችን ምረጥ(ጪ)።
- የእደጥበብ ሥራን ትርጉም ለማዳበር እና የእጅ ሙያን ለማሻሻል ግብረመልስ/ምላሽ አስተያየትን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ለለውጥ ምላሽ ለመስጠት የእደጥበብ ሥራን ፍጠር(ሪ)።
- እምነትን፣ እሴትን፣ ወይም ባህርይን ለመለወጥ ስነጥበብ እንዴት እንደሚጠቀም አስረዳ(ጂ)።

**የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ**

- የሥነጥበብ ሥራን በመምረጥ በአርቲስቱ/ቷ አገላለጽ መሠረት እንዴት የአውደርዕይ መስፈርት እንደሚያሟላ ግለጽ(ጪ)።

- የእደጥበብ ሥራን ለተለየ አውደርዕይ ስፍራ/ቦታ ለማቅረብ አመቺ/ተገቢ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- ከጊዜ ወደ ጊዜ የእደጥበብ ሥራ እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ የሚያሳዩ በግል የተሰበሰቡ የስነጥበብ ውጤቶችን አስረዳ(ጂ)።
- አጽንኦት/ትኩረት የስነጥበብ ሥራህ(ሽ)ን ዝርዝር - ግምገማ እንዴት እንደሚለውጥ አስረዳ(ጂ)።
- የስነጥበብ ስራን በዝርዝር መገምገም የመነሻ ትርጉሙን እንዴት እንደሚለውጥ አስረዳ(ጂ)።
- በግል የታቀደ የስነጥበብ ሥራ ግቡን መትቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ መስፈርት መርጠህ(ሽ) ተጠቀም(ሚ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ዝንባሌ/ምላሽ መስጠት

- ከተለያዩ ባህሎች ሙዚቃ ውስጥ ሙዚቃዊ ፎርም መግለፅ።
- የአንድ የሙዚቃ ክፍል ሞድ በጆሮ ሲቀርብ ሜጀር ወይም ማይነር መሆኑን መለየት።
- የሙዚቃ ንጥረነገሮች ለተለያዩ የአለም ባህሎች በጆሮ ናሙናዎች እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ መግለፅ።
- መስፈርቶችን ማዳበር እና የራሳቸውን እና የሌሎችን አፈፃፀም ለመገምገም ተግባራዊ ማድረግ።

### ሙዚቃ መጫወት

- ከፍ ባለ ድምፃዊ አገላለፅ/አወጣጥና በግልፅ ቋንቋ እና የዱድ/ከአጋር ጋር ጣእመ ዜማ ያላቸውን መዝሙሮች በትክክል መዘመር።
- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይም ተነፃፃሪ ክፍሎችን ሲጫወቱ፣ ቀላል የባለ-ክር መሳርያ ማሳየት/ማቅረብ።
- በቡድኖች ውስጥ ሆኖ መዘመር፣ተምቡሮችን በመደባለቅ እና ዳይናሚክ ደረጃዎችን በማጋጠም።
- ባህላዊ ዘፈን እና ባህላዊ ጭፈራዎችን ከተለያዩ የአለም ባህሎች ማቅረብ።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከአለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከአጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- አንድ ቀላል ዜማ በትሬብል ስታፍ በተለያዩ ቁልፎች በሶልፌጅዮ ወይም በተመጣጣኝ ስርኣት ማንበብና መጫወት።
- ሚዛኑን በጠበቀ ኖታ በመጠቀም አንድ አጭር ዜማዊ ሃረግ ከቃል ፅሁፍ ኖታ መውሰድ።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- ለክፍል ውስጥ መሣሪያዎች ጣዕመዜማ አዘጋጅ(ጂ)።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### የግልና የማህበራዊ ሃላፊነት

- ለበለጠ ግኝት ግስጋሴን እየተቆጣጠሩ የግል እንቅስቃሴ ግቦችን መመስረትና ማሻሻል።
- የጊዜ አስተዳደር ስልቶችን በብልሃት መተግበር።

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- የራስ-በራስ-መገምገም እና ግብረመልስ በመንቀሳቀስ ክሂሎቶች መሻሻል አስፈላጊነታቸውን ማወቅ።
- በስተላይ-የተወረወረን ነገር መያዝ ማሳየት።
- በመያዝ፣ መግፋት፣ እና መወርወር ላይ የሚያስፈልጉ ክሂሎቶችን ማጣራት።
- በአካል ክፍሎችና በመሳርያዎች ለመምታት ተፈላጊ ክሂሎቶችን ማሻሻል።

## የጤና ትምህርት

### የግልና የተጠቃሚ ጤና (PCH)

- ለደህንነትና፣ ለይበልጥ ጤናማ ህይወቶች የጤና አደጋዎችን ለመቀነስ ጤና-አራማጅ ስነምግባሮችን መለየትና መለማመድ።
- የተጠቃሚን የጤና ጉዳዮችና አገልግሎቶች የሚመለከቱ ዋጋ ያላቸው የጤና መረጃዎችን የሚያቀርቡ መገልገያዎች ከቤትና ከት/ቤት ፈልጎ ማግኘት።

### ደህንነትና ጉዳት

- ወደ ዉስጥ በትንፋሽ በመሳብ ሊበላሹ የሚችሉ የመኖርያ ቤት ውጤቶችን መለየት።
- ፆታዊ ወከባን እንደ ሁከት አይነት እውቅና መስጠት።